የሚዲያ መግለጫ

አፍሪካ ሂውማኒታሪያን አክሽን ለአህጉሪቱ መሪዎች ጥሪ አቀረበ። ዘላቂ ልማትን ማራመድ፣ የመፈናቀል መንስኤዎችን መፍታትና አህጉራዊ ሰብአዊ ምላሽን ማጠናከር

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ - የካቲት ፯ ፳፻፲፯

የአፍሪካ ሕብረት የመሪዎች 38ኛ መደበኛ ጉባኤን ምክንያት በማድረግ የአህጉሪቱ መሪዎች በአዲስ አበባ ኢትዮጵያ እየተሰባሰቡ ባለበት ወቅት አባል ሀገራት የመፈናቀል መንስኤዎችን ለመፍታት ቆራጥ እርምጃዎች እንዲወስዱ እና አህጉራዊ ሃብትን ለሰብአዊ አገልግሎት ተደራሽነት እንዲያውሉ አፍሪካ ሂውማኒታሪያን አክሽን (Africa Humanitarian Action (AHA) ጥሪ ያቀርባል።

አፍሪቃ ከ45 ሚሊዮን በላይ በግዳጅ የተፈናቀሉ ዜጎች መገኛ በመሆኗ፣ የስደተኞችን፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን እና የጥገኝነት ጠያቂዎችን ጨምሮ፣ አህጉሪቱ በግጭት፣ በፖለቲካ አለመረጋጋት፣ በአየር ንብረት ለውጥ እና በኢኮኖሚ ችግር ምክንያት የከፋ ሰብዓዊ ቀውስ ገጥሟታል። እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የአፍሪካ ሕብረትና በአፍሪካ ሀገራት ክልላዊ መፍትሄዎች እና በተቀባይ ማህበረሰብ ድጋፍ አጋርነታቸውን አሳይተዋል። ነገር ግን፣ ያለው አስገዳጅ ሁኔታ እንደሚያሳየው፣ የበለጠ ጠንካራና፣ የተቀናጀ ተግባር-ተኮር ጥረቶች በአስቸኳይ ያስፈልጋሉ።

መፈናቀል የሰብአዊነት ጉዳይ ብቻ አይደለም - በዋናነት በአስተዳደር መዛባት፣ በልማት ጉድለት እና በጸጥታ ችግሮች ላይ የተመሠረተ ቀውስ ነው። አፍሪካ ሂውማኒታሪያን አክሽን የአፍሪካ መሪዎች በአህጉሪቱ ውስጥ ያለውን ጦርነት እና ግጭቶች ለማስቆም ከልብ ጥረት እንዲያደርጉ ያሳስባል፡፡ ዘላቂ ሰላምን፣ አካታች አስተዳደርን ማረጋገጥ እና ከመነሻው የመፈናቀልን ችግር የሚያስወግድ ኢኮኖሚያዊ እድሎችን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ለዚህም አሕጉራዊ ድርጅታችን እና አባል ሀገራቱ አግባብነት ያላቸውን የአፍሪካ ሕብረት መመሪያዎችን እና ፖሊሲዎችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ በተለይም በሚከተሉት ተግባራት ላይ ያተኮሩ ጥረቶችን እንዲያደርጉ እናሳስባለን።

1. **የግጭት መከላከልና አፈታት ዘዴዎችን ማጠናከር** - የአስተዳደር ጉድለቶችን፣ የፖለቲካ መገለልንና በሀብት ላይ የተመሰረቱ ግጭቶችን፣ በአፍሪካ የሰላም ግንባታ እና እርቅ ጥረት መፍታት፤
2. **አህጉራዊ የሰብዓዊ ድጋፍን ማሳደግ** - በዓለም አቀፍ ለጋሾች ዘንድ መሰላቸት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ እና በቅርቡ ደግሞ የአሜሪካ የውጭ ዕርዳታ መቆሙን ተከትሎ አፍሪካ የአህጉሪቷን ሀብቶች በማሰባሰብ ለድንገተኛ አደጋ ዝግጁነት ምላሽ፣ መልሶ ለመቋቋም አቅም ግንባታ እና ለተፈናቀሉ ማህበረሰቦች ዘላቂ መፍትሄዎችን በማሰባሰብ በውጭ ዕርዳታ ላይ ጥገኛነትን መቀነስ፤
3. **የአፍሪካ ህብረት የካምፓላ ስምምነትን ተግባራዊ ማድረግ** - የተፈናቃዮችን መብት የሚያስጠብቁ ፖሊሲዎችን ማስከበር እና በግዳጅ መፈናቀልን የሚፈጽሙ ወንጀለኞችን ተጠያቂ ማድረግ፤
4. **የአየር ንብረትን የመቋቋም ስልቶችን ያዋህዱ** - በአየር ንብረት ምክንያት የሚፈጠረውን መፈናቀል ለዘላቂ ኑሮ፣ ለቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓቶችና በአካባቢ ጥበቃ ላይ በማዋል እያደገ የመጣውን ተፅዕኖ መቋቋም።

አህጉር በቀል የሆነው አፍሪካ ሂውማኒታሪያን አክሽን፣ ከሰላሳ ዓመታት በላይ በሃያ አፍሪካ ሀገራት ለብዙ ሚሊዮን ስደተኞችና ተፈናቃዮች የምግብ፣ የትምህርት፣ የህክምናና የመጠለያ አገልግሎት ከአፍሪካ ሕብረት፣ ከተባበሩት መንግስታትና ከሌሎች አጋሮች ጋር በመተባበር እርዳታ አቅርቧል፡፡ በአፍሪካ ውስጥ ላሉ የተለያዩ መፈናቀል ተግዳሮቶችን ምላሽ ለመስጠት፣ የሰብዓዊ ቁርጠኝነትን ወደ እውነት ለመቀየር የፖለቲካ ፍላጎት እና ተጨባጭ እርምጃዎች የአፍሪካ መሪዎች እንዲወስዱ አፍሪካ ሂውማኒታሪያን አክሽን ይጠይቃል፡፡

የአፍሪካ መሪዎች የአህጉሪቱን ሰብአዊ ፍላጎቶች ለማሟላት ሀገር በቀል መፍትሄዎችን ለማግኘት ጉዳዩን በጥልቀት ለመፍታት የተወሰነ ቀን እና ቦታ እንዲወስኑ ይጠይቃል።

የአፍሪካውያን የመፈናቀል ችግር ለመቅረፍ አፍሪካውያን የመፍትሄ ሃሳቦችን የሚያገኙበት ጊዜ አሁን ነው፣ ይህም በራስ የመተማመን፣ አህጉራዊ አብሮነት እና የአፍሪካ ህዝቦች የመላው አፍሪካ ፕሮጀክት ዋና ዋና ዓላማዎች እንዲነለብቱ በማሰብ ነው።

ᔕᔕᔕᔕᔕᔕᔕᔕᔕᔕᔕᔕᔕᔕᔕᔕᔕᔕᔕᔕᔕᔕᔕᔕ

ለሚዲያ ጥያቄዎች፣

AHA Communications፣ communications@africahumanitarian.org
+251 116 604800፣ www.africahumanitarian.org

መጨረሻ